# REGULATION MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅነት ያላቸው ሠነዶች፦** ABA, ABC, ABC-RA, ACA, ACD, ACG, ACG-RA, ACG-RB, DNA, ECM, ECM-RA, FAA, JEE, JEE-RA
**ኃላፊነት የሚመለከተው ቢሮ፦** Division of District Operations

**ስለ ትምህርት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች እቅድ**

I. **አላማ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲ FAA ስለትምህርት ህንጻዎች እቅድመተግበር

የትምህርት ህንጽዋዎችን አቅም የማሳደግ ፍላጎትን ምላሽ ለመስጠት፣ የቦታ መረጣን ጨምሮ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ እና የት/ቤት መዘጋት እና/ወይም ጥምረት የካፒታል ኢንቨስትመንት ፕሮግራም (CIP) የማስፋት እና የማሳደግ ሂደት፣ የትምህርት ህንጻዎች ማስተር ፕላን፣ እና ስለ ተንቀሳቃሽ ንብረት ስትራተጂዎችን ለመተለም

II. **ዳራ**

በቦርድ ፖሊሲ FAA ስለ ትምህርት ህንጻዎች እቅድላይ እንደተደነገገው፣ የትምህርት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች እቅድ አካል የሚያካትተው፦

A. ስለተማሪዎች ምዝገባ የሚጠበቅ ግምት እና የትምህርት ህንጻዎች እና የህንፃ ሲስተሞችን የሚገኙበትን ሁኔታ ግምገማና ትንታኔ፣

B. በትምህርት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አስተዋጽኦ፤ እና

C. ምላሽ ሰጪ አማራጮችን የሚፈጥሩ እና ወደ ትክክለኛና ፍትኃዊ የፋይናንስ ኃላፊነት እና ትርጉም ያላቸው ውሳኔዎች የሚመራ የዉሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ፣ ከአካባቢ፣ ከስቴት፣ እና ከፌደራል መስፈርቶች ጋር የሚሣለጡ፣ የቦርድ ፖሊሲን ACA ፀረ-መድሎአዊነት፣ ሚዛናዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት የሠፈነበት የቦርድን ፍትሃዊነት እና ሚዛናዊነት ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

III. **ትርጉም**

A. አዋሳኝ ት/ቤቶች ማለት ቢያንስ በአካባቢዉ የሚገኙ የድንበር ተጋሪነት ያላቸዉ ት/ቤቶች ናቸው።

B. የካፒታል ባጀትማለት ለካፒታል ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተመደበ ዓመታዊ ባጀት ነው።

C. የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም (CIP)ለካፒታል ማሻሻያዎች የሚውል የስድስት-ዓመት አጠቃላይ የወጪ እቅድ ነው። CIP ቦታ መረከብ፣ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ ግንባታ፣ እና የህዝብ ት/ቤቶች ህንጻዎች ጥገና፣ ካውንቲ አቀፍ የሲስተሞችን የመተካት ፕሮጀክቶች እና ትላልቅ ካፒታል ፕሮጀክቶችን ያካተተ ተግባር ላይ ያተኩራል። CIPው በያንዳንዱ የጎደሎ ቁጥር ኣመት የሚጀምር ለስድስት ኣመት እድሜ የሚያገለግል ሆኖ በየሁለት-ኣመት ሂደት ኣማካይነት ተገምግሞ ይፀድቃል። ለባለሙሉ ቁጥር የበጀት አመቶች፣ በፀደቀው CIP አፈላጊ ለውጦች የባለ-ስድስት-ኣመት CIP ወቅት የማሻሻያ ለውጦች በሁለተኛው ኣመት ይደረግባቸዋል።

D. የከተማ አስተዳደር ቡድኖች ማለት ዜጋ፣ የቤት ባለቤት፣ ጎረቤት፣ ወይም በሜሪላንድ ብሔራዊ ካፒታል ፓርክ እና ፕላን ኮሚሽን (M-NCPPC) ወይም በሞንትጎመሪ ሪጅናል አገልግሎት ማእከሎች የተመዘገቡ የከተማ ነዋሪዎች

ማህበራትን ይመለከታል።

E. ክለስተር/Clusterየሁለተኛ ደረጃ፣ አንደኛ ደረጃ፣ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያካተተ ወደዚያ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገቡ ግልጽ የሆነ ጂኦግራፊያዊ የት/ቤቶች ምደባ ማለት ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወደ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተከፋፈለ የምደባ ቅጥ አላቸው፣ በአንድ ወይም የበለጠ ክለስተሮች ዉስጥ አንዳንድ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተከፋፈለ የምደባ ሁኔታ ይኖራቸዋል።

F. ኮንሰርትየም ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን ወይም መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችን እንደየቅርበታቸው ተማሪዎች በተወሰነ አይነት የትምህርት አሰጣጥ ወይም በዝንባሌአቸው በሚመርጡት ቦታ የሚማሩበትን እድል ለመስጠት በተደራጀ ሁኔታ የተካለሉ ናቸው።

G. የትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊቲ ዲዛይንየትምህርት ቤት ህንጻ ግንባታ ድረስ ያሉትን ሁሉንም የእቅድ እና የዲዛይን ሂደቶችን ያካትታል። እንደሁነቶቹ ቅደምተከተል፣ የትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊቲ ዲዛይን አፈጻጸም እንደሚከተለው ይሆናል፦

1. የትምህርት ዝርዝሮች የሚያስፈልጋቸውን የማስተማር ፕሮግራም ለመደገፍ የሚያስፈልገውን ያህል የቦታ ስፋት እና ስለህንጻው አቀማመጥ እና የዲዛይን ዝግጅት አርኪቴክቱን ይመራል።

2. የአዋጭነት ጥናት ስለ ፕሮጀክቱ መጠን እና የዋጋ ግምት የሚገልጽ ሲሆን፣ ስለ ፋሲሊቲው ዲዛይን ዝርዝር አይኖረውም።

3. ስዕላዊ ንድፍ/Schematic design ማለት ጽንሰ ሐሳቦችን ለት/ቤቱ የመነሻ እቅድ የሚያመለክት እና የሚያዳብር የዲዛይን የመጀመሪያው ምዕራፍ አካል ነው።

4. የመጀመሪያ ደረጃ ዕቅዱ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ስፋት፣ ስኬል፣ የአጠቃቀም ግንኙነት፣ የትራፊክ ፍሰት እና የፕሮጀክት ኮምፖነንቶችን ዋጋ ይገልጻል። የፅንሰ-ሀሳብ ዲዛይኑ በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የታሰበውን ህንጻ የውጪ እና የውስጥ ገጽታዎችን፣ የውስጥ እና የውጪ ቁሳቁሶችን የመዋቅር፣ የመካኒካል፣ የቧንቧ እና የኤሌክትሪክ ስርዓት ፅንሰ-ሀሳቦችን በማካተት ግልጽ እና አጠቃላይ ምስል ያሰጣል። የመጀመሪያው ፕላን እንዲፀድቅ ለቦርድ ቀርቧል።

5. ዲዛይን ማጎልበት ማለት የአርኪቴክቸራል እቅዶቹን የማጣራት እና የፕሮጀክቱን መካኒካል፣ ኤሌክትሪካል፣ እና የቧምቧ ስራዎችን ሲስተም የመሣሰሉት የፕሮጀክቱ መሠረተ ልማት ስራዎች የሚዳበሩበት ደረጃ ነው።

6. የግንባታ ሠነዶች ፋሲሊቲውን ለመገንባት የተዘጋጁ በንድፍ ስራዎቹ ውስጥ የተካተቱ የግንባታ ዝርዝሮችን የያዘ ሲሆን ህንጻውን ለመገንባት እንደ ኮንትራት ሠነድነት መጠቀሚያ ዝርዝር ሠነዶች ይኖሩታል።

H. ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምርጫ ምደባ ዕቅዶች ተማሪዎች በፕሮግራም አቅርቦት ምክንያት ወይም በዝንባሌአቸው ላይ በመመስረት ለትምህርት ቤት ምደባ ምርጫቸውን መግለጽ የሚችሉባቸውን ጂኦግራፊያዊ አካባቢን(ዎች) ይለያሉ። እነዚህ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች፣ በተወሰኑ መስፈርቶች ተማሪዎችን በት/ቤቱ ለመቀበል ዋስትና ሊያገኙ የሚችሉባቸው "base areas/መነሻ አካባቢዎች" ተብለው የሚጠሩ አካባቢዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ወይም አካባቢው "base areas" የሌለው አንድ ነጠላ ቦታ ሊሆን ይችላል።

I. የወላጅ መምህር (ተማሪ) ማህበራት (PT(S)As) የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ወላጆች አስተማሪዎች ማህበራት (MCCPTA) አባል ቡድኖች ናቸው። PT(S)A ሳይኖር፣ በትምህርት ቤት የሚሰራ የወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ እና ተማሪዎች ድርጅት PT(S)A የሚተካ ይሆናል።

J. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ በቦርድ ፖሊሲ FAA ዓላማ መሠረት የትምህርት ቤት ህንጻዎች እቅድ፣ እና ይህ ደንብ፣ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ለትምህርት ቦርዱ ስለ ት/ቤቶች እቅድ አማራጮች የሚኖራቸውን ተጽእኖ ለማሳወቅ፣ ግብዓቶችን ለመፈለግ የተነደፉ ሂደቶችን የሚያመለክት ሲሆን ይህም በቦርድ ፖሊሲ ABA፣

የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ እና የቦርድ ፖሊሲ FAA፣ የትምህርት ቤት ህንጻዎች እቅድ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፣ ተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ የማህበረሰብ አባላትን እና ድርጅቶችን እና የአካባቢ መንግስት ኤጀንሲዎችን ጨምሮ ሰፊ ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል።

## IV. የፋሲሊቲዎች/የትምህርት ቤት ህንጻዎች እቅድ ትንታኔ

የትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች እቅድ ዝግጅት ሂደት በሚከተለው አኳኋን ይጀምራል፦

A. የሚመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት ትንበያ

1. የተማሪዎች ምዝገባ ትንበያዎች የሚዘጋጁት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፕላኒንግ ዲፓርትመንት የካውንቲ ህዝብ ብዛት ትንበያ እና ከሌሎች ተዛማጅ የእቅድ ምንጮች ጋር በቅንጅት ነው።

2. በእያንዳንዱ የመኸር ወቅት (ፎል)፣ ለእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የስድስት ዓመታት የምዝገባ ትንበያዎች ይዘጋጃሉ። የረዥም-ጊዜ ትንበያዎች ታሳቢ የሚያደርጉት 10ኛ እና 15ኛ ዓመት በተከታታይ የሚመዘገቡትን ታሳቢ በማድረግ ነው። የረዥም ጊዜ ትንበያዎች ዝርዝር የትንታኔ ክፍሎች ማለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ክለስተር ወይም ኮንሰርትየም ትንበያ ነው።

3. ትንበያዎችን ለማጥራት እና በአገልግሎት አሰጣጥ፣ በፕሮግራሞች፣ ወይም በሠራተኞች ምደባ ላይ ማናቸውንም ለውጦች ለማንፀባረቅ በየዓመቱ ኤፕሪል ወር ስለ ቀጣዩ የትምህርት ዓመት የትምህርት ቤት ምዝገባ ትንበያዎች ክለሳ ይደረጋል።

4. በሥራ የዋለው የተማሪዎች ምዝገባ ትንበያ ዘዴ CIP እና ማስተር ፕላን ሰነዶች ጋር አባሪ ተደርጎ ቀርቧል።

5. ለትምህርት ቤቶቹ የሚመረጡት የምዝገባ ክልሎች በትምህርቱ ቤት የሚማሩ ተማሪዎችን ሁሉ ያካትታሉ።

   a) ለትምህርት ቤቶች የሚመረጡት የመመዝገቢያ ክልሎች ስፋት —

      (1) በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 450 እስከ 750 ተማሪዎች፣

      (2) በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 750 እስከ 1,200 ተማሪዎች፣ እና

      (3) በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 1,600 እስከ 2,400 ተማሪዎች።

      (4) በልዩ እና አማራጭ የፕሮግራም ማዕከላት ውስጥ መመዝገብ ከላይ ከተጠቀሱት ሊለይ ይችላል እና በአጠቃላይ ዝቅተኛ ነው።

   b) አዳዲስ ትምህርት ቤቶች ሲታቀዱ ወይም በነባር ትምህርት ቤቶች ላይ ለውጦች እንዲኖሩ ሲደረግ የምዝገባ መጠን ግምት ውስጥ ይገባሉ። ሁኔታዎች ካስገደዱ የምዝገባ ብዛት መጠን የተለየ ሊሆን ይችላል።

6. የትምህርት ቤት ተማሪዎች ስብጥር ፕሮፋይልእና የትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊት ፕሮፋይል

   a) የትምህርት ቤት የተማሪዎች ስብጥር ፕሮፋይል የትምህርት ቤቱን የተማሪዎች የዘር/የጎሳ ስብጥር፣የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ አገልግሎት (FARMS) እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማዳበር (ELD) ፕሮግራሞች ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች % መቶኛ እና የትምህርት ቤት የመያዝ አቅምን ያካትታል።

b) የትምህርት ቤት ህንጻ ፋሲሊቲ ፕሮፋይል የክፍል አጠቃቀም በፕሮግራም እና ስኩዌር ፉቴጅ፣ የቦታ ስፋት፣ የተከፈተበት ዓመት፣ ለፓርኮች ያለው ቅርበት እና ለማዘዋወር የሚያስችሉ የማስተማሪያ ክፍሎችን ቁጥር ያካትታል።

B. የትምህርት ፕሮግራም መስፈርቶች

1. የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የህንጻዎች አስተዳደር ክፍል ሰራተኞች በትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ ክፍል እና በማስተማር እና መማር ክፍል ካሉት የትምህርት ፕሮግራም ሰራተኞች ጋር ተባብረው በመስራት ለትምህርት ፕሮግራሞች የህንጻ/ፋሲሊቲ መስፈርቶችን ልየታ ያደርጋሉ።

2. የሚገመቱት የፕሮግራም መስፈርቶች የክፍል መጠን ለውጦችን እና ነባር፣ አዲስ፣ እና የታቀዱ የትምህርት ፕሮግራሞች ለውጦችን እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶችን ግምት ውስጥ ያስገባሉ።

C. የፕሮግራም አቅም ስሌት

1. የፕሮግራም አቅም መጠን በፋሲሊቲው ይካሄዳል ተብሎ በተገመተው የትምህርት ፕሮግራሞች መሠረት በፋሲሊቲው የሚማሩ ተማሪዎችን ቁጥር ያመለክታል። MCPS የፕሮግራም ስፋት (የመያዝ ችሎታ) የሚሰላው በአንድ ት/ቤት ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ክፍሎችን እያንዳንዱ መማርያ ክፍል መያዝ የሚችለውን የተማሪዎች ብዛት እና ፕሮግራም በንፅፅር ነው።

2. የተማሪዎች ብዛት በመማሪያ ክፍል የመያዝ አቅም ሲሰላ ምጥጥኑ በዓመታዊ የሥራ ማስኬጃ በጀት ሂደት የሚወሰኑ የሰራተኞች ምደባ ምጥጥን ጋር መምታታት የለባቸውም።

3. በቦርድ ውሳኔ በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ የፕሮግራሙ አቅም እና የመማሪያ ክፍል መያዝ የሚችለው የተማሪዎች ብዛት መመሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

***በመማሪያ ክፍል የተማሪዎች ብዛት ምጥጥን መመሪያ***

| ደረጃ | በመማርያ ክፍል የተማሪዎች ብዛት ንፅፅር |
|---|---|
| ሄድ ስታርት እና ቅድመ-መዋኣለ ህፃናት | 40:1 (በቀን 2 ክፍለ-ጊዜዎች) |
| ሄድ ስታርት እና ቅድመ-መዋኣለ ህፃናት | 20:1 (በቀን 1 ክፍለ-ጊዜ) |
| K ክፍል (መዋአለ ህጻናት) | 22:1 |
| K ክፍል-የክፍል መጠኑ ይቀንሳል | 18:1 |
| 1ኛ እስከ 2ኛ ክፍሎች—የክፍል መጠናቸው ይቀንሳል | 18:1 |
| 1ኛ እስከ 5ኛ ክፍል (ኤሌሜንታሪ) | 23:1 |
| 6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት<br>9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 25:1[a]<br>25:1[b] |
| ልዩ ትምህርት፣ ELD፣ ተመራጭ ፕሮግራሞች | ከዚህ በታች "c" ይመልከቱ |

a) የፕሮግራምን በሚመለከት አቅም በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የጊዜ ሠሌዳ መጨናነቅን ለማስወገድ ይስተካከላል። 25 ተማሪዎችን የመያዝ አቅም ያለው መደበኛ የመማርያ ክፍል እጅጉን ተመራጭ የሚሆነው የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ፋሲሊቲ .85 ይባዛል (በመማርያ ክፍል 21.25 ተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል)።

b) የፕሮግራም አቅምን በሚመለከት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የጊዜ ሠሌዳ መጨናነቅን ለማስወገድ ይስተካከላል። 25 ተማሪዎችን የመያዝ አቅም ያለው መደበኛ የመማርያ ክፍል እጅጉን ተመራጭ የሚሆነው የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፋሲሊቲ .90 ይባዛል (በመማርያ ክፍል

22.5 ተማሪዎች ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል)።

c) ልዩ ትምህርት፣ ELD፣ አማራጭ ፕሮግራሞች፣ እና ሌሎች ስፔሻል ፕሮግራሞች ከተዘረዘሩት የተለየ የክፍል ምጥጥን ሊኖራቸው ይችላል።

D. የትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊቲ አጠቃቀም የፕሮግራም አቅምን፣ ከስቴት የደረጃ ምደባ አቅም፣ እና ተማሪዎችን ለመቀበል ከሚኖረው አቅም ጋር በወቅቱ ያለውን የፋሲሊቲ አጠቃቀም እና የታለመውን የተማሪ ምዝገባ ትንተና ንጽጽር ያመለክታል።

1. የፋሲሊቲ አጠቃቀም ደረጃ 80 ፐርሰንት ያነሰ እንደሆነ የትምህርት ቤት ጠቀሜታው አነስተኛ ነው ተብሎ ይታሰባል።

2. የፋሲሊቲ አጠቃቀም ደረጃ 100 ፐርሰንት የሚበልጥ ከሆነ የትምህርት ቤቱ አጠቃቀም ከመጠን በላይ እንደሆነ ይገመታል።

3. በልዩ ሁኔታ በቦርድ ካልተወሰነ በስተቀር፣ ኤለመንተሪ፣ መካከለኛ ደረጃ፣ እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የፕሮግራም አቅም 80 እስከ 100 ፐርሰንት ዉጤታማ የፋስሊቲ አጠቃቀም መተግበር አለበት።

a) ከመጠን በላይ አጠቃቀምን በሚመለከት፣ አዲስ ግንባታ ከመታቀዱ አስቀድሞ የቦታው አጠቃቀም ለረዥም ጊዜ አስፈላጊ ስለ መሆኑ ለመገምገም ጥረት ይደረጋል።

b) የፋሲሊቲዎች አጠቃቀም ዝቅተኛ የመሆንም ሁኔታ ከረዥም ጊዜ የተማሪዎች ምዝገባ ትንበያ አንፃር ይገመገማል።

4. ቋሚ ስፋ ያለ ኣማራጭ እስከሚገኝ ድረስ የተማሪዎች ምዝገባ እድገት ከጨመረ ተዘዋዋሪ የመማርያ ክፍሎች በጊዜያዊነት ኣገልግሎት ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

5. ተዘዋዋሪ የመማሪያ ክፍሎች የህፃናት እንክብካቤ ፕሮግራሞች በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲቆዩ ለማስቻል ሊያገለግሉ ይችላሉ፣ እና ሌሎች ተጨማሪ አጠቃቀሞችንም ለማስተናገድ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ተዘዋዋሪ የመማርያ ክፍሎች ከሌሎች የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መማርያ ክፍሎች ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጤና እና የደህንነት ደረጃ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

E. በስቴት የተደነገገ የአቅም ደረጃ (SRC) በሜሪላንድ ስቴት የተደነገገው አንድ ት/ቤት ሊቀበላቸው የሚችል የተማሪዎች ቁጥር ስቴቱ ባስቀመጠው የተማሪ ብዛት- ለ-ክፍል እና በትምህርት ቤት የማስተማሪያ ክፍሎች ብዛት መሆን እንዳለበት ይገልጻል። ለካፒታል ፕሮጀክቶች የስቴት ባጀት ለማግኘት ብቁነትን ለመወሰን ስቴቱ SRC ይጠቀማል። SRC የማስተር ፕላን እና CIP አባሪ ተደርገው ለት/ቤቶች ተሰጥተዋል።

F የትምህርት ቤት ቦታ ስፋትማለት እንደሚከተለው የትምህርት ፕሮግራምን በሙሉ ለማስተናገድ የሚያስፈልግ ያክል ኤከሬጅ ነው፡-

1. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች—7.5 ኤከር ጥቅም ላይ የሚውል የቦታ ስፋት ያለው ሲሆን ሌሎች መስፈርቶችን ጨምሮ የማስተማሪያ ፕሮግራሙን አሟልቶ ለማከናወን የሚያስችል መሆን አለበት። 7.5 ኤከር መስፈርት የተመሠረተው ሁነኛ በሆነ ክፍት ቦታ ላይ ሲሆን፣ መጠኑ እንደ ቦታዉ ይዘት፣ በዙሪያዉ ባሉት የቦታ ገደቦች፣ በጂኦግራፊያዊ አካባቢ ላይ ሊኖር የሚችል የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና እቅድ ውስጥ በሚካተቱት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

2. መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች—የሚፈለገው ጥቅም ላይ የሚውል የቦታ መጠን ቦታው ማሟላት ያለበትን መስፈርቶችን ጨምሮ የትምህርት ፕሮግራሙን ለመተግበር የሚያስችል 15.5 ኤከር ነው።15.5 ኤከር መስፈርት የተመሠረተው ሁነኛ በሆነ ደልዳላ ክፍት ቦታ ላይ ሲሆን፣ የቦታ ስፋቱ መጠን እንደ ቦታዉ ይዘት ሁኔታ፣ በዙሪያዉ ባለው የቦታ እጥረት ሁኔታ፣ በአካባቢው ላይ ሊኖር የሚችል

ጂኦግራፊያዊ የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና ለመሥራት እቅድ ውስጥ በሚካተቱት ነገሮች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

3. ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች — ለማስተማር ፕሮግራም የሚመጥን፣ የቦታ ስፋት መስፈርትን አካቶ ቢያንስ 35 ኤከር ቢሆን ይመረጣል።35 ኤከር መስፈርት የተመሠረተው ሁነኛ በሆነ ደልዳላ ክፍት ቦታ ላይ ሲሆን፣ መጠኑ እንደ ቦታዉ ይዘት፣ በዙሪያዉ ባለው የቦታ እጥረት፣ በአካባቢ ላይ ሊኖር የሚችል ጂኦግራፊያዊ የቦታ እጥረት፣ የህዝብ ብዛት፣ እና ለመሥራት ቅድ ውስጥ በሚካተቱት ነገሮች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል።

G. የህንጻ/የፋሲሊቲ ሁኔታ ጠቋሚ መረጃ (FCI) ጣሪያዎች፣ ግድግዳዎች፣ መስኮቶች፣ ማሞቂያ፣ አየር ማናፈሻ እና የአየር ማቀዝቀዣ (HVAC) የመሳሰሉትን የህንጻው ዋና ዋና የግንባታ ሲስተሞች አገልግሎት የሰጡትን ያህል ጊዜ እና ዋጋ ያሰላል። FCI የአንድን ሕንፃ አጠቃላይ ሁኔታ ለመገምገም ይጠቅማል፤ ይህም ለመማር እና ስራ ለመሥራት ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ነው። MCPS 2025-2026 የትምህርት አመት FCI መነሻ ይሆናል። የመሠረት መነሻው አንዴ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በየጊዜው FCI በተደጋጋሚ ወቅታዊ ይደረጋሉ። እነዚህ ወቅታዊ መረጃዎች ለህዝብ ይፋ ይደረጋሉ።

## V. የክለስተር አስተያየቶች

A. በየዓመቱ ጁን ወር፣ የክለስተር ተወካዮች የትምህርት ቤቶቻቸውን ግንባታ ሂደት በተመለከተ ለአካባቢው PT(S)A አመራር፣ ርእሰ መምህራን፣ እና ከማህበረሰቡ ጋር በመመካከር የተሰማቸውን ማንኛውንም ስለ ግንባታው ያስተዋሉትን ስጋቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ወይም ሀሳቦችን ጭምር ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት ማቅረብ ይችላሉ።

B. የክላስተር አስተያየቶች CIP ውስጥ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት በሚሰጡት ሪኮመንዴሽን መሠረት ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

## VI. ስለ ፋሲሊቲ እቅድ የውሳኔ አሰጣጥ ማእቀፍ

A. በየዓመቱ፣ አዳዲስ የተማሪዎች ምዝገባ ትንበያዎች ከተዘጋጁ እና ከላይ የተቀመጡ ሌሎች ትንታኔዎች ከተጠናቀቁ በኋላ፣ የክላስተር አስተያየቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች መሻሻል ያለባቸውን የተቋማትን ፍላጎቶች በማሟላት ረገድ ፕሮጀክቶችን እየለዩ ቅድሚያ ይሰጣሉ። CIP የውሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ ፍትሃዊ እና ውጤታማ የሪሶርስ ኢንቨስትመንትን ማረጋገጥ በርካታ ነገሮችን ያካትታል። እነዚህ መመዘኛዎች አንድ ላይ ሆነው በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ ስለ ካፒታል ኢንቨስትመንቶች አጠቃቀም በመረጃ ላይ የተመሰረተ፣ ግልጽ እና ስትራቴጂካዊ ውሳኔዎችን ለማድረግ የሚያስችል ማዕቀፍ ይፈጥራሉ። ቁልፍ የሆኑ ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

1. የህንጻው/የፋሲሊቲው ሁኔታ ጠቋሚ መረጃ:- ከላይ እንደተገለጸው የአንድ ሕንፃ አካላዊ ሁኔታ እና ዋና ዋና ሲስተሞቹ።

2. ለትምህርት መስጫነት ያለው ተስማሚነት:- ህንጻው ዘመናዊ የማስተማሪያ ልምዶችን እና የፕሮግራም መስፈርቶችን የሚያሟላበት ደረጃ።

3. ጥራት ያለው የተማሪዎች ፍላጎቶች:- የተማሪዎች ልዩ ፍላጎቶች፣ ልዩ ፕሮግራሞች፣ እና የድጋፍ አገልግሎቶችን ጨምሮ።

4. የህንጻው/የፋሲሊቲው አጠቃቀም:- ከፕሮግራሙ አቅም ጋር ሲነጻጸር መያዝ የሚችለው የተማሪዎች ብዛት ትንበያ።

B. ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ከተቀመጡ በኋላ፣ ሰራተኞች በቦርድ ፖሊሲ FAA፣ የትምህርት ተቋማት እቅድ ላይ ለተቀመጡት የተቋማት ፍላጎቶች እና የአቅም መስፈርቶች ምላሽ ለመስጠት ምርጡን አማራጭ ይወስናሉ። ለትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊቲ ፍላጎቶች እና የአቅም መስፈርቶች ምላሽ የመስጠት አማራጮች የሚያካትቱት—

1. ትምህርት ቤቶችን በተፈላጊው ጥሩ ሁኔታ ለማቆየት ጠቃሚ የሆኑ እና የጠቀሜታነታቸውን እድሜ ለማራዘም ለምሳሌ፡- ሙቀት መስጫ፣ የአየር ማናፈሻ፣ የአየር ሁኔታ ማስተካከያ፣ እና መካኒካል ሲስተሞችን፣ ጣራዎችን፣ እና በርካታ ሌሎች የህንጻ እና መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን ካውንቲ-አቀፍ ሲስተም የመተካት ፕሮጀክቶች፣ እና

2. የህንጻዎችን አቅም ለመጨመር የተወሰኑ ፕሮጀክቶችን የሚያካትቱ ዋና ዋና የካፒታል ፕሮጀክቶች፤ ነባር ተቋማትን ጥገና ማድረግ፣ ማደስ፣ ማስተካከል፣ በሌላ ጥቅም ላይ እንዲውል ማዘጋጀት ወይም መተካት፤ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ህንጻዎች ያለውን ቦታ ለመጠቀም ማሻሻል። እንደዚህ ዓይነት የፕሮጀክት አማራጮች አዲስ ፋሲሊቲ መገንባትን ወይም ባለው ፋሲሊቲ ላይ ተጨማሪ ግንባታ ማድረግን ያካትታል።

B. የህንጻ ሁኔታዎችን እና የአቅም መስፈርቶችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ አማራጮች፣ እንደአስፈላጊነቱ፣ ዝቅተኛ አቅም ባላቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ የምዝገባ መጠን ለመጨመር እና/ወይም ከአቅም በላይ ተማሪዎች ካሏቸው ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ዝውውር ለማሣለጥ ካፒታል በጀት በማያስፈልግ ስልት የአቅም ማስተካከያዎችን ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ይህም የሚከተሉትን የሚያካትት ሲሆን፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደሉም—

1. የድንበር ለውጦች፣ ወይም

2. ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምርጫ ምደባ ዕቅዶች፤ እና/ወይም

3. የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም መጣመር።

C. የውሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፉ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት የሚቀርብ የአርክቴክት ምርጫ፣ የህንጻው ዲዛይን፣ እና ሌሎች ከህንጻው ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ ማስገባትንም ሊያካትት ይችላል።

## VII. የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም

A. በየዓመቱ ፎል ላይ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ ዓመታዊ የካፒታል በጀት እና የስድስት-ዓመት CIP ወይም ቀደም ሲል የተወሰነውን CIP ማሻሻያዎችን አስተያየቶች/ሬኮመንዴሽኖችን ይፋ ያደርጋል።

B. በተጨማሪ፣ ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ድንበሮችን፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምደባ እቅዶች፣ ት/ቤት መዘጋት እና/ወይም ማጣመር፣ እና ማናቸውም ሌላ የትምህርት ቤት ህንጻ/ፋሲሊቲ እቅድ አስተያየቶች ማህበረሰቡ እንዲመለከተው ይበልጥ ጊዜ ስለሚያስፈልግ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

C. የስድስት ዓመት CIP የሚከተሉትን ያካትታል፡-

1. የቦርድ ግምገማ እና እርምጃ የመውሰድ ስርአት፡-

a) ተገቢው የትምህርት ቤቱ የምዝገባ/ተማሪዎችን የመቀበል አቅም

b) የፕሮግራሙ አቅም እና የህንጻ አጠቃቀም ስሌት

c) ትምህርት ቤቱ ያረፈበት ቦታ መጠን

2. ስለተማሪዎች የአቀባበል ግመታ አሠራር ዳራ

3. የወቅቱ የተማሪዎች ምዝገባ መጠን፣ የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ስብጥር ሁኔታ፣ እና የፋሲሊት አጠቃቀም ሁኔታ

4. የፕሮግራሙ አቅም እና የፋሲሊት አጠቃቀም ትንታኔ

5. አንደኛ ደረጃ (ኤለመንተሪ ስኩል)፣ መካከለኛ ደረጃ (ሚድል ስኩል)፣ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የምዝገባ ትንበያ ለእያንዳንዱ የስድስት-ዓመት እና የመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 10 እና 15 ዓመት የረዥም-ጊዜ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ትንበያ።

6. እርምጃ እንዲወሰድ የቀረበ ምክረሃሳብ፣ የትምህርት ቤትን አቅም መለወጥ፣ አዳዲስ ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች፣ ትላልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶች፣ የፕሮግራም ቦታዎች፣ እና/ወይም ትምህርት ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት አይነት።

7. ካውንቲ አቀፍ የመዋቅሩን ፕሮጀክቶች መርሃ ግብር በየፈርጁ፣ በተወሰኑ ትምህርት ቤቶች ዋና/ትልልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶችን፣ CIP እና ማስተር ፕላን ምዕራፍ 1 ላይ የተገለጹት አዳዲስ ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች።

8. በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት አማካይነት የካፒታል በጀት ምደባ ይዘት አጠቃላይ ሪኮመንዴሽን

D. በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ያስፈልጋሉ ተብለዉ ከታመኑ CIP ተጨማሪ መረጃዎችን በማቅረብ ማሟያዎችን ሊገለፁ ይችላሉ

E. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚያቀርቧቸው CIP አስተያየቶች MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ። ለቦርድ አባላት እና ለቦርድ ሠራተኞች፣ MCPS ሥራ አስፈጻሚዎች፣ እና MCCPTA ፕሬዚደንት፣ የአካባቢ MCCPTA ም/ፕሬዚደንቶች እና የክለስተር አስተባባሪዎች CIP ሠነዶችን ያገኛሉ። በተጨማሪ፣ CIP ሠነዶች እና በኦንላይን የሚገለጹ ጽሑፎች ለርእሰመምህራን፣ PT(S)A ኃላፊዎች፣ ለማዘጋጃ ቤቶች፣ እና ለሲቪል ቡድኖች ይደርሳቸዋል። ይህ ማሳወቂያ የቦርዱን የስራ ክፍለጊዜዎች፣ የማህበረሰብ ውይይት መድረኮች፣ እና CIP የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ያካትታል።

F. የቦርድ CIP የግምገማ እና የአፈጻፀም እርምጃ የጊዜ ሰሌዳ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ክፍለ ጊዜዎችን እና የማህበረሰብ ውይይት መድረኮችን ከኖቬምበር መጀመሪያ እስከ አጋማሹ ድረስ፣ እና ከኖቬምበር አጋማሽ እስከ ኖቬምበር መገባደጃ ድረስ ተግባራዊ ማድረግን ይገልጻል። (ስለ ማህበረሰብ አስተያየት ሂደት ሰክሽን XI.B እና ስለ አመታዊ ካለንደር ሰክሽን XII ይመልከቱ።)

G. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት ስለ CIP ማናቸውም የተለየ የእቅድ ጉዳዮችን እና/ወይም ማሻሻያዎችን ምክረ ሀሳብ ፌብሩወሪ አጋማሽ ላይ ያቀርባሉ። ስለ እነዚህ ጉዳዮች የቦርዱ የጊዜ ሠሌዳ ላይ አንድ ወይም የበለጠ የሥራ ክፍለጊዜዎችን እና ፌብሩወሪ/ማርች ላይ አንድ ወይም የበለጠ የማህበረሰብ ውይይቶችን እና ኤፕሪል ላይ ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል። አስፈላጊ ከሆነ፣ በእቅድ የተለዩ ጉዳዮች የጊዜ ቅደምተከተልን በሚመለከት በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት አማካይነት ለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በቂ ጊዜ ለመስጠት እንዲመች ይሻሻላል።

H. ያልተጠበቁ ሁኔታዎች መኖራቸውን ቦርዱ በሚያረጋግጥበት ጊዜ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ CIP ምክረ ሀሳቦችን ለመስጠት፣ ስለፋሲሊቲ ስራዎች እቅድ፣ ስለቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምርጫ አመዳደብ እቅዶች፣ ወይም ትምህርት ቤትን መዝጋት እና/ወይም ማጣመር አማራጭ የጊዜ ሠሌዳ ያዘጋጃል።

I. ቦርዱ ገምግሞ እርምጃ ከወሰደ በኋላ፣ ቦርዱ የሚጠይቀው CIP፣ በጠቅላላ የተጠየቀውን የካፒታል ፕሮጀክቶች መግለጫ ቅጾችን ጭምር (PDFs)፣ እንዲመለከቱት እና እንዲጸድቅ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል እና ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ሥራ አስፈጻሚ ይቀርባል። ቦርዱ የሚጠይቀው CIP ለመረጃነት ወደ M-NCPPC ይላካል።

J. የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ ሃሳቦች በአጠቃላይ የካውንቲ CIP ውስጥ እንዲካተቱ ጃንዋሪ 15 ለካውንቲ ካውንስል ይቀርባሉ። ከቦርድ-በተጠየቀው CIP የካውንቲው ካውንስል የግምገማና የውሳኔ እርምጃ የሚወስድበት የጊዜ ገደብ ከፌብሩወሪ እስከ ሜይ ድረስ ነው።

K. ሜይ መገባደጃ ላይ የካውንቲው ካውንስል በየሁለት ዓመት የሚዘጋጅ የስድስት-ዓመት CIP ማሻሻያዎችን

ይወስናል።

## VIII. የትምህርት ፋሲሊቲዎች ማስተር ፕላን (MASTER PLAN)

A. በየዓመቱ ጁላይ ላይ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለ ትምህርት ቤት ህንጻዎች አቅም መስፈርቶችን እና አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ፋሲሊቲዎችን የካውንቲ ካውንስል ያፀደቃቸውን የካፒታል በጀት እና ቦርድ ያፀደቃቸው ሌሎች ካፒታል ያልሆኑ ስትራቴጂዎችን ጠቅላላ ዘገባ ይፋ ያደርጋሉ። ይህ ሰነድ፣ የትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች ማስተር ፕላን (ከዚህ በኋላ ማስተር ፕላን ተብሎ የሚጠራው)፣ በስቴቱ የህዝብ ትምህርት ቤቶች የግንባታ ፕሮግራም ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት አስፈላጊ ናቸው።

1. ማስተር ፕላኑ፡- በካውንቲው ካውንስል ስለ ገንዘብ ድጋፍ የጸደቁ ሁሉም የካፒታል ፕሮጀክቶች የሚኖራቸውን ተገማች ተጽእኖ እና በቦርዱ የጸደቁ የህንጻዎችን አቅም መስፈርቶች እና የመገልገያ ፍላጎቶችን ለማሟላት ማንኛውንም ካፒታል ያልሆኑ ስትራተጂዎችን ያካትታል።

2. እንደ CIP በተመሣሣይ ማስተር ፕላኑ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   a) መስፈርቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

      (1) አስፈላጊ የሚሆነው የተማሪዎች ምዝገባ መጠን (ተማሪዎችን የመቀበል አቅም)

      (2) የፕሮግራምን የማስተናገድ አቅም እና የኣጠቃቀም ስሌት

      (3) ት/ቤቱ የሚሠራበት ቦታ ስፋት

   b) የምዝገባ ትንበያን የሚመለከት ዳራ መረጃ

   c) በወቅቱ ያለው የተማሪዎች ምዝገባ ቁጥር፣ የትምህርት ቤቱ የተማሪዎች ስብጥር መግለጫ እና የህንጻዎቹ/የፋሲሊቲዎቹ የአገልግሎት እድሜ እና አቅም መግለጫ

   d) ፕሮግራሙን የማስተናገድ አቅም እና የኣጠቃቀም ስሌት

   e) በሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት ለእያንዳንዱ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምዝገባ ትንበያዎች፣ እና ለመካከለኛ እና ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 10ኛ እና 15ኛ ዓመት የረጅም ጊዜ ትንበያዎች። ይህ መረጃ ቀደም ባለዉ ፎል ላይ የተደረገዉን ትንበያ ከአንድ-ዓመት የስፕሪንግ ትንበያ ጋር፣ እና በድንበር ለውጦች፣ የተማሪ ምርጫ ጂኦግራፊያዊ የምደባ እቅዶች፣ የት/ቤት መዘጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ቦርድ በሚደነግገው ሌሎች ለውጦች ሳቢያ የሚከሰቱ ማናቸውንም የተማሪዎች ምዝገባ/የመቀበል አቅም ትንበያ ለውጦችን ማንፀባረቅ አለበት።

   f) የካውንቲ ካውንስል-ያፀደቀውን PDF ሁሉንም የካፒታል ፕሮጀክቶች ከጊዜ ሠሌዳ ጋር፣ የዋጋ ግምት፣ እና የገንዘብ ምንጮች

## IX. የረዥም ጊዜ እቅድ

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የረዥም-ጊዜ (ማለት፡- ከስድስት-ዓመት የዘለለ CIP ጣልቃ መግባት) ስለ CIP የዝግጅት ማእቀፍ MCPS ወደፊት እንዲያስብበት እና በፔዳጎጂ ከዳበሩ የፋሲሊቲ አማራጫች እና ለትምህርት ፕሮግራሞች የፈጠራ አቀራረብ፣ እንዲሁም የመማሪያ ክፍል መጠን ለውጦች፣ ከመደበኛው የተለዩ ቦታዎችን ስለመጠቀም፣ እና ሌሎች ተገቢ ወይም ተስማሚ አቀራረቦችን ይጠቀማል።

B. እነዚህ የረዥም-ጊዜ ሁኔታዎች ማእቀፍ በሪጅናል ወይም በክለስተር ደረጃ፣ አራት የእድገት ማኔጅመንት ሁኔታዎችን

ግምት ውስጥ በማስገባት የፋሲሊቲ እቅድ የሚያስከትለውን ተፅእኖ ይዳስሳሉ፡-

1. ከፍተኛ ተማሪዎችን የመቀበል/የምዝገባ እድገት
2. መካከለኛ/ዝቅተኛ ተማሪዎችን የመቀበል/የምዝገባ እድገት
3. ተማሪዎችን የመቀበል/የምዝገባ እድገት የማይኖር ከሆነ
4. ተማሪዎችን የመቀበል/የምዝገባ ሁኔታ እየቀነሰ ከሆነ

C. አንድ ትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤቶች ምን ያህል ወይም ለወደፊት ከልክ ያለፈ አጠቃቀም ወይም አነስተኛ ጥቅም ላይ እንደሚውል ስለማንኛውም ሁኔታ ትንታኔው ላይ መገለጽ አለበት። ከእነዚህ ትንታኔዎች የሚመነጩት አማራጮች በአንፃሩ በዚህ ሳይወሰን፣ የሚከተለውን የረዥም-ጊዜ ስልት ይዳስሳሉ፡-

1. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚደረጉ ለውጦች፣ ቦታው፣ ወይም የፕሮግራሞች ብዛት፣ ተማሪዎችን የመቀበል/የምዝገባ ሁኔታ እና የመማሪያ ክፍል መጠን፣ የክፍል አደረጃጀት፣ ወይም ዋናዎቹ የጊዜ ሠሌዳዎች
2. የህንጻዎችን አካላዊ አቅም መጨመር
3. ጥቅም ላይ ያልዋሉ ያሉትን ቦታዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ወይም ለመደበኛ አጠቃቀም እንዲውል ማድረግ

D. ስለ ረዥም ጊዜ የፋሲሊቲ ዕቅድ ጉዳዮች እና ስትራቴጂዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰብ ባለው የበለፀገ ልምድ እና እውቀት ላይ በመመርኮዝ ከስድስት-ዓመት ያለፈ CIP የጊዜ ማዕቀፍ ነገር ግን 10 - 15 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የጊዜ ማእቀፍ የሚያስፈልጋቸውን ባለብዙ ፈርጅ የትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎች እና እቅድ በሚመለከቱ ጉዳዮች የማህበረሰቡን ራዕይ በሚመለከት ስለ ትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች እና እቅድ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ለማማከር የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የት/ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች አማካሪ ኮሚቴ ያቋቁማል። የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ከማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ግብአት ጋር የፋሲሊቲ አማካሪ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል።

## X. ከተወሰኑ መገልገያዎች ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሂደት መመሪያዎች

A. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ መመሪያዎች

1. በተለይም ስለሚከተለው የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች-ጋር የተገናኘ እቅድ መሣካት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝነት አለው፡-

   a) ለአዲስ ትምህርት ቤቶች የቦታ መረጣ

   b) የትምህርት ቤት ክልሎች/ድንበር

   c) ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች

   d) የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም መጣመር

   e) የፋሲሊቲ ዲዛይን

   f) በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የተለዩ ሌሎች ከትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች

ጋር - የሚገናኙ ጉዳዮች

2. ከቦርድ ፖሊሲ ABA፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ፣ እና የቦርድ ፖሊሲ FAA፣ የትምህርት ተቋማት እቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ፣ MCPS ሰክሽን V.A.1 ላይ በተገለጹት ሂደቶች መሠረት በሰራተኞች የተዘጋጁ የፋሲሊቲ አማራጮች ላይ ስለሚኖረው ተጽእኖ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንትን ለማማከር የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ያስፈልጋል።

a) የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ግብአቶችን ለመጠየቅ እና ቀጥታ ያሉትን እድሎች ለማሳወቅ – መረጃዎችን ይፋ ያደርጋል

(1) ከበርካታ ባለድርሻ አካላት አስተዋጽኦ፣

(2) ከሚመለከታቸው ማህበረሰቦች ሰፋ ያለ ተሳትፎ፣ እና

(3) የተለያዩ በርካታ አመለካከቶች።

b) በእቅድ አወጣጥ ሂደት ላይ የቅድሚያ ባለድርሻ መሆን ያለባቸው ሁኔታው በቀጥታ የሚነካቸው/የሚመለከታቸው ወላጆች/ሞግዚቶች፣ ሠራተኞች፣ እና ተማሪዎች ናቸው። MCCPTA፣ የአካባቢ PT(S)As፣ ወይም ሌላ ወላጅ/ሞግዚት ወይም የተማሪ ቡድኖች፣ MCPS የሥራ ኃላፊዎች ጋር፣ የሚመለከታቸው የከተማ አስተዳደር፣ የአካባቢ የመንግስት አስተዳደር ኤጀንሲዎች፣ የከተማ ነዋሪዎች፣ እና ሌላ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች እንደአግባቡ ተጨማሪ ባለድርሻ አካላት ሆነው ይካተታሉ።

c) የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጎልበት ሠራተኞች በርካታ የኮሙኒኬሽን ስልቶችን ይተገብራሉ።

(1) ባለድርሻ አካላትን የማሳተፍ ስልት እንደሂደቱ ባህሪ፣ መጠን፣ እና ስፋት ሊለያይ ይችላል።

(2) የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በዚህ አያበቃም፣ አጠቃላይ የትምህርት ሥርአቱን የሚመለከቱ ኮሚቴዎችን ወይም አማካሪ ቡድኖችን፣ የትኩረት ቡድኖች፣ የሥራ ግብረኃይል፣ የሥራ ቡድኖች፣ የውይይት ቡድኖች፣ ግብአት የመሰብሰብ ዳሰሳዎች፣ በቴክኖሎጂ የታገዙ ግንኙነቶች፣ እና/ወይም ሌላ የማህበረሰብ የእቅድ ዝግጅት ክፍለጊዜዎች፣ እንደ ቻርት የመሣሠሉ ፍላጎት ባላቸው መካከል ስለሚደረጉ ትብብሮች ዲዛይን የተደረጉ ወይም ስለሚመለካተቸው ክፍሎች እና ለሠራተኞች መረጃ እና ግብረመልስ የሚሰጡ ነገሮችን ያካትታል።

(3) በማናቸውም ጊዜ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ሠራተኞች የዳሰሳ ጥናት፣ ወይም በቴክኖሎጂ የሚታገዝ ግንኙነት ወይም በሌላ ዘዴ ህዝባዊ መድረኮችን እንዲጠቀሙ መመሪያ ይሰጣል።

B. ስለ ትምህርት ቤቶች ድንበር/ማካለል እና ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ አማራጭ እቅዶችን ስለማዳበር ተጨማሪ መመሪያዎች

1. ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉበት የተለዩ አማራጮች ከመቅረባቸው አስቀድሞ፣ ስለ ትምህርት ቤት ክልሎች ለውጥ እና/ወይም በአካባቢው ስነምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት በካውንቲው ተፅእኖ የሚኖረው ጂኦግራፊያዊ የሆነ በተማሪ ምርጫ የሚደረግ ምደባ እቅዶችን የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ለቦርድ ምክረሃሳብ ያቀርባል።

2. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በርካታ ምዕራፎች ያሉት በመጀመሪያ ደረጃ መከናወን ያለባቸውን ዝርዝሮች ትንተና በማድረግ ቅድሚያ መሰጠት ያለበትን በቦርድ ፖሊሲ FAA ላይ የተገለጹትን አራት ምክንያቶችን ያገናዘበ አፋጣኝ ምላሽ መሰጠት ያለበትን ያቀርባል፣ ከዚያም በስነምድራዊ አቀማመጥ

ያሉት አካባቢ(ዎች) ሙሉ በሙሉ ስለ ትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድበቦርድ ፖሊሲ FAA ላይ የተገለጹትን አራት ዋና ዋና ምክንያቶች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ምክረሃሳቦችን ያዘጋጃል።

a) በተለይም፣ በትምህርት ቤት ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ላይ የሚኖረው ተጽእኖ የተገመተው የካፒታል ፕሮጀክት (ለምሳሌ፡- የትምህርት ቤቱን አቅም 20 ፐርሰንት ባነሰ የሚጨምር ወይም በትምህርት ቤት አካባቢ ላይ መጠነኛ ለውጥ ብቻ የሚያደርግ) ከሆነ ምላሽ ለመስጠት ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል የትምህርት ቤት ክለስተር ክልል፣ እና/ወይም ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ የምደባ እቅድ ትምህርት ቤቱ የሚገኝበትን ክለስተር ብቻ እና ከክለስተሩ ውጪ በአቅራቢያ የሚያዋስኑ ትምህርት ቤቶች ላይ ተጽእኖ በሚያደረግ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል።

b) በሰፊው ማህበረሰብ ላይ ተጽእኖ እንደሚያሣድር የሚታመንበት አስፈላጊ ጉዳይ የአጎራባች ክለስተሮችን ማህበረሰቦች ተሳትፎ ማስፋት አማራጭ ግንዛቤ ይፈጥራል።

3. የትምህርት ቤቶች ሰ‍ፐርኢንተንዳንት ፋሲሊቲዎች ጋር የተገናኙ ጥረቶችን በተመለከተ ለቦርድ ምክረሀሳብ ከማቅረባቸው አስቀድሞ በእርግጠኝነት ተጽእኖ የደረሰባቸውን ማህበረሰቦች መለየት ያስፈልጋል።

4. የትምህርት ቤትን ክልል እና/ወይም ትኩረት የተሰጣቸው የመልከአ ምድራዊ አቀማመጥ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅዶችን ቦርዱ ለይቶ ካስቀመጠ በኋላ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፉ በፖሊሲ FAA ላይ በተገለጹት አራት ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ በርካታ አማራጮችን ያዘጋጃሉ፣ የትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲዎች እቅድ እና እያንዳንዱ አማራጭ እነዚህን ሊያራምዱ የሚችሉበትን ምክንያታዊነት መግለጫ ይሰጣል፡-

a) የተማሪ ማህበረሰብ ስብጥር ባህርይ

በቦርድ ፖሊሲ FAA መሠረት፣የትምህርት ቤት ህንጻዎች/ፋሲሊቲ እቅድ፣ አማራጭ ትንታኔዎች በአጠቃላይ በተጎዱት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አማራጮች ከግምት ዉስጥ ያስገባሉ። ከእያንዳንዱ የሚመለከተው ትምህርት ቤት የቦርድ ፖሊሲ ACD መሠረት የተለያየ የተማሪዎችን ብዝሃነት የመፍጠር አማራጮች ላይ መተኮር አለበት፤ ይኼምበጥራት ላይ ያተኮረ ትምህርትማለት ነው። ይህ ማለት በሚመለከታቸው ትምህርት ቤቶች የተማሪ ማህበረሰብ ስብጥር እና የአካባቢ ስነምድራዊ አቀማመጥ መካከል ያለው የጎላ ልዩነት በማናቸውም ሌላ ምክንያት ሊረጋገጥ የማይችል ቁልፍ ምክንያት ይሆናል። የተለያዩ አማራጮች የሚያስከትሉትን ተጽእኖዎች የሚያመለክት የተማሪ ማህበረሰብ ስብጥር ውሂብ የሚከተሉትን ያካትታል፡- የተማሪዎችን የዘር/የጎሣ ስብጥር፣ የተማሪውን ህብረተሰብ ማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ደረጃ፣ እና በሌሎች አሳማኝ የሆኑ ልዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ተሳትፎ ያለው የተማሪዎች ስብጥር አመላካች ሁነቶች ማለት ነው። በሚቀርቡት አማራጮች ላይ እነዚህ ጉዳዮች ስለ ስብጥር በተገለጹት መረጃዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ግምት መሰጠት አለበት።

b) ጂኦግራፊ

MCPS በልጆቻቸው ትምህርት ቤቶች የቤተሰብ ተሳትፎን በሚመለከት በሚያደርገው ትኩረት መሰረት፣ አማራጮች፣ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ትምህርት ቤቶች ከሚገለገሉባቸው ማህበረሰቦች ጋር ያላቸውን ጂኦግራፊያዊ ቅርበት፣ እንዲሁም የመግባቢያ፣ የትራፊክ፣ የመጓጓዣ ሁኔታ (የህዝብ መጓጓዣ ጨምሮ) የመሬት መልክዓምድራዊ አቀማመጥን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። የዚህ ትንታኔ አካል ተደርጎ፣ ወደ ትምህርት ቤት የእግር ጉዞ እና ለመጓጓዣ ያለው ርቀት መታየት አለበት። በተጨማሪ፣ አማራጮቹ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ክለስተር ያሉትን ብቻ ሳይሆን ቢያንስ ከክልል ውጭ በአዋሳኝ የሚገኙትን ትምህርት ቤቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

c) የትምህርት ቤት ምደባዎች ፀንተው የሚቆዩበት ጊዜ

አማራጮጭ ምደባዎቹ በተቻለ መጠን ለረዥም ጊዜ ዘለቄታ ያላቸው ውጤት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። እነዚያኑ ተመሣሣይ ተማሪዎች የሚመለከት ተማሪዎችን እንደገና ምደባ ሲደረግ በቅርብ የተደረገ የድንበር ወይም ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅድ ለውጦችን፣ እና/ወይም የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም መጣመር ትኩረት መሰጠት አለበት።

d) የፋሲሊቲ አጠቃቀም

የትምህርት ቤት ክልል-ድንበር እና ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች በፋሲሊቲ አጠቃቀሞ በተቻለ መጠን በረዥም ጊዜ 80 ፐርሰንት እስከ 100 ፐርሰንት ውጤታማ በሚሆን ደረጃ ላይ መተኮር አለበት። በማህበረሰቡ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅእኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ፋሲሊቲን ከአንድ ክላስተር በላይ በጋራ የመጠቀም ፕላን በአንዳንድ ሁኔታዎች በጣም ውጤታማ ፕላን ሊሆን ይችላል። እቅዶቹ በተቻለ መጠን የካፒታል እና የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ለመቆጠብ የሚያስችል ኃላፊነት የተሞላበት መሆን አለባቸው።

5. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በሚጠናቀቅበት ደረጃ ላይ ሲደርስ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ስለተጠቀሙበት የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሂደት፣ ሠራተኞች ያዘጋጇቸው አማራጮች፣ እና የባለድርሻ አካላት ግብረመልስን የሚያካትት ነገር ግን በዚህ ያልተገደበ አጭር መግለጫ ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የሚቀርብ ሪፖርት ያዘጋጃሉ።

6. በተጨማሪ፣እንደአስፈላጊነቱ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ማናቸውንም የተናጠል PT(S)A አመለካከት አስተያየቶችን መቀበል ይችላል።

7. ለቦርዱ የሚቀርቡ ምክረሃሳቦች በሚዘጋጁበት ወቅት፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ስለተገለጹት ስለ እያንዳንዳቸው ሰክሽን X.B.2 እና X.B.4. ላይ በተገለጸው መሠረት የሚታይ እና ምክንያታዊ የሆነ ውጤት እንደሚያመጣ አመክንዮ መስጠት አለበት።እያንዳንዳቸው ምክንያቶች ታሳቢ ቢደረጉም፣ እያንዳንዱን/ሁሉንም የቀረቡትን አስተያየቶች ከሁሉም ምክንያቶች ጋር ለማገናዘብ አይቻልም ይሆናል።

8. ይህ መመሪያ እንደዚሁ በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተለይተው የሚቀርቡ ሌሎች ከፋሲሊቲ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ እንደአግባቡ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል።

C. አዲስ የትምህርት ቤት ቦታ አማራጮችን ስለማጎልበት ተጨማሪ መመሪያዎች

በቦርድ ፖሊሲ FAA ላይ ከተገለጸውየትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ፣ በስጦታ ወይም በግዢ የተገኙ እና የቦርድ ኢንቬንቶሪ ላይ የተመዘገቡ አዲስ የትምህርት ቤት ቦታዎችን ጨምሮ በሚገመገሙበት ጊዜ በተጨማሪ የሚከተሉት ምክንያቶች ተገናዝበው ታሳቢ ይደረጋሉ።

1. የተማሪ ማህበረሰብ ጂኦግራፊያዊ ስፍራው ከነባር ወይም የወደፊት ት/ቤቶች ጋር ሲገናዘብ
2. ስፋት በኤከር ሲለካ
3. የመሬት መልክአምድራዊ አቀማመጥ እና ሌሎች አካባቢያዊ ሁኔታዎች
4. የመገልገያዎች (ውሃ፣ ኤሌክትሪክ፣ ወዘተ) መኖር
5. አካላዊ/ፊዚካል ሁኔታ
6. የቦታ መኖር እና ለመረከብ የሚወስደው ጊዜ
7. የግል ንብረት ከሆነ ቦታውን ለማግኘት የሚያስፈልገው ዋጋ

D. የፋሲሊቲ ዲዛይን/ንድፍ

የትምህርት ፋሲሊቲ ዲዛይኖች በአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ መርህ እና በወቅቱ የትምህርት ፕሮግራም ፍላጎት፣ እንዲሁም ለወደፊት ታሳቢ በተደረገ የፕሮግራም ፍላጎት መሠረት ጤናማ እና ሰላማዊ አካባቢን የሚጠብቁ መሆን አለባቸው። የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚያስፈልገው አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት በሚያመራ ሂደት ወይም እንደሚከተለው በነባር ህንፃዎች ላይ የሚደረግ ተጨማሪ ግንባታ ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ነው፡-

1. የትምህርት ዝርዝሮች የሚገልጹት የማስተማር ፕሮግራምን ለመደገፍ ምን ያህል ቦታ እንደሚያስፈልግና ስለህንጻው አቀማመጥ እና ዲዛይን ዝግጅት የንድፍ ባለሙያውን ይመራል። MCPS የእቅድ ሰራተኞች የታቀዱትን ፕሮጀክቶች የትምህርት ዝርዝሮች የሚዘጋጁት ከትምህርት ፕሮግራም ሰራተኞች እና ከተጎዱት ትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራን እና ሰራተኞች ጋር በመተባበር ነው።

2. የዲዛይን አማራጮች የሚቀረጹት ትምርታዊ ዝርዝሮችን በመገምገም የመጀመሪያ ዲዛይን ለመስራት በተመረጠ አርቲኬት(ቶች) አማካይነት ነው። የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሚሰበሰበው ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

    a) ስለ ካፒታል ፕሮጀክቶች ዲዛይን የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ለማጎልበት የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች የተለያየ አይነት ስትራቴጂዎችን ይተገብራሉ።

    b) የማህበረሰብ ቡድኖች ተወካዮች፣ የከተማ አስተዳደር፣ የካውንቲ የመንግስት አስተዳደር (የሞንትጎመሪ ካውንቲ የፕላን መምሪያ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፓርኮች መምሪያ)፣ እና አዋሳኝ የንብረት ባለቤቶች ካሉ፣ ለአዲስ ትምህርት ቤት ሥራ ዲዛይን በሚዘጋጅበት ወቅት እና በነባር ህንፃ ላይ ለሚጨመር ዲዛይን ወይም ለነባር ትምህርት ቤቶች ትልልቅ የካፒታል ፕሮጀክቶች ዲዛይን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

3. የመጀመሪያውን ዲዛይን ያካተተ የመጀመሪያው እቅድ እንዲፀድቅ ለቦርድ ይቀርባል።

E. የትምህርት ቤት መዘጋት ወይም መጣመር

ከላይ ሰክሽን X.B.4 ላይ ከተገለጹት ምክንያቶች በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤት መዘጋት እና ማጣመር ሲያስፈልግ ስለ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ የሜሪላንድ ህግ መስፈርቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## XI. ከትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት በሚቀርቡ ምክረሃሳቦች ላይ የሚወሰድ የቦርድ እርምጃ

A. ቦርዱ ከላይ ሰክሽን VII ላይ እንደተጠቀሰው የትምህርት ቤቶችን ሱፐርኢንተንደንት ምክረሃሳብ ለመገምገም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ክፍለ ጊዜዎችን ያካሂዳል።

1. ቦርዱ፣ በአብላጫ ድምጽ፣ የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት ስለ ቦታ ምርጫ፣ ስለ ትምህርት ቤት ክልል፣ ለተማሪዎች ምርጫ የጂኦግራፊያዊ ምደባ ዕቅዶችን፣ ወይም የትምህርት ቤቶች መዘጋት እና/ወይም መጣመር አማራጭ ምክረሃሳቦችን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል።

2. በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ትርጉም ያለው ማሻሻያ በአብዛኛው የቦርድ ኣባላት የሚደገፍ ኣማራጭ መሆን አለበት። በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳብ ቀደም ብሎ ያልተካተተ በማንኛውም ት/ቤት ማህበረሰብ ላይ ተፅእኖ የሚያደርግ ማንኛውም ማሻሽያ ትርጉም ያለው ማሻሽያ ተብሎ ይታመናል። ቦርዱ የሚያቀርባቸው አማራጮች በቦርድ ፖሊሲ FAA "ሰክሽን G" ላይ ከተገለጹት ምክንያቶች አንዱን ወይም አብላጫውን ይተገብራል የትምህርት ፋሲሊቲዎች እቅድ።

3. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳቦች እና በቦርድ-የሚቀርቡ ኣማርጮች በቦርዱ የመጨረሻ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ለማህበረሰብ አስተያየት የሚሰጥበት መድረክ መቅረብ ኣለባቸው። በማንኛውም የስራ ክፍለጊዜ የቀረበው ኣማራጭ በቦርዱ ተቀባይነት ካገኘ፣ ስለቀረበው ኣማራጭ የህዝብ ኣስተያየት ለመስማት በማከታተል የማህበረሰብ ውይይት መድረክ መዘጋጀት ኣለበት።

4. ይሄኛው ተግባር የማህበረሰብ አስተያየት በተሰጠበት እቅድ ላይ ትርጉም ያለው ተፅእኖ የማይፈጥር ከሆነ በት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ወይም ከቦርድ-በተጠየቀ አማራጭ ላይ ቦርዱ መጠነኛ ማሻሻያዎችን የማድረግ ነፃነት አለው። ያለ በቂ ማስታወቂያ እና የሚመለከታቸው ማህበረሰቦች አስተያየት የመስጠት እድል ሳይኖራቸው የቀረቡት አማራጮች በቦርድ የስራ ክፍለጊዜ ግምት ውስጥ አይገቡም።

B. የቦርድ የማህበረሰብ አስተያየት መቀበያ ሂደት

1. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንትን CIP አስተያየቶችን ተከትሎ በየዓመቱ የማህበረሰብ አስተያየት መቀበያ ሁነቶች ይካሄዳሉ። በተጨማሪ፣ ስለ ቦታ ምርጫ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪዎች ምርጫና ምደባ እቅዶች፣ ወይም የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ማጣመርን በሚመለከት እርምጃዎች ከመወሰዳቸው አስቀድሞ የህዝብ አስተያየት መስጫ የውይይት መድረኮች ይካሄዳሉ።

   a) የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት የሚያቀርቡትን የካፒታል ባጀት እና የስድስት - ዓመት CIP ይፋ ከተደረገ በኋላ በመቀጠል የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮች ኖቬምበር ላይ ይካሄዳሉ።

   b) ቀደም ሲል ለህዝብ ይፋ ያልተደረጉ የሱፐርኢንተንደንት አስተያየቶች ካሉ ፌብሩወሪ መገባደጃ ወይም ማርች ላይ የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው የውይይት መድረኮች ሊካሄዱ ይችላል።

   c) ያልተለመዱ ሁኔታዎች መከሰታቸውን ቦርዱ ካመነበት እና የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንዳንት የተለየ እና/ወይም አስተያየት ለማቅረብ ያጠረ መርሃ ግብር የሚያስፈልግ ከሆነ በአመቱ ውስጥ በሌሎችም ጊዜያት የማህበረሰብ ውይይቶች ይካሄዳሉ።

2. ከሌሎች የተሳትፎ መንገዶች በተጨማሪ፣ የማህበረሰብ አባላት ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና ለቦርድ በጽሑፍ በሚደረጉ ግንኙነቶች፣ የህዝብ አስተያየቶችን፣ እና ምስክርነቶችን አስተዋጽኦ የማድረግ እድሎች አሏቸው።

3. የከተማ አመራር ቡድኖች፣ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ እና በህዝብ የተመረጡ ሃላፊዎች በህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮች ላይ ምስክርነት ሊሰጡ ይችላሉ።

4. MCCPTA ክለስተር አስተባባሪዎች፣ ከአካባቢ PT(S)A ፕሬዚደንቶች ጋር በመማከር፣ በማህበረሰብ ውይይት ላይ በክለስተር የታቀፉ ትምህርት ቤቶችን በመወከል ምስክርነቶችን እንዲያስተባብሩ እና የምስክርነት መርሃ ግብር ሲያዘጋጁ የተለያዩ ሃሳቦችን እንዲቀርቡ ይበረታታሉ። ለያንዳንዱ ክላስተር ፕሮግራም ምስክርነት የሚሰጥበት ወቅት የሚደራጀው በተቻለ መጠን PT(S)A ድርጅታዊ ክለስተር ("quad-clusters") እና/ወይም በኮንሶርቲየም ነው።

5. የፅሁፍ አስተያየቶች ከማህበረሰቡ በማንኛውም ወቅት ተቀባይነት ይኖራቸዋል። ነገር ግን ትኩረት የሚሰጣቸው አስተያየቶች በቦርዱ እርምጃ ሳይወሰድ አስቀድሞ ቢያንስ 48 ሰኣት በፊት ወደ ቦርዱ መድረስ አለባቸው።

6. በማህበረሰብ ውይይት መድረኮች ላይ ለመናገር/ምስክርነት ለመስጠት ለሚፈልጉት የጊዜ ሠሌዳ ለማዘጋጀት የቦርድ ጽ/ቤት ኃላፊነት ነው።

   a) በትምህርት ቦርድ መመሪያ መጽሐፍ ላይ እንደተገለጸው CIP ውይይቶች፣ ተማሪዎች፣ የከተማ አስተዳደር፣ እና MCCPTA በቅድሚያ አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ በመቀጠልም PT(S) እና እንደየቅደምተከተላቸው ግለሰቦች እና የከተማ/ነዋሪዎች፣ ካውንቲ አቀፍ ድርጅቶች ሀሳባቸውን መስጠት ይችላሉ።

   b) በህዝብ የተመረጡ ኃላፊዎች በአጀንዳዉ ላይ ለመናገር ራሳቸው የሚመርጡት ሠዓት ይመደብላቸዋል።

c) በቦርዱ የሃሳብ መስጫ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር፣ ድርጅቶች፣ የከተማ አስተዳደሮች፣ እና በህዝብ የተመረጡ ኃላፊዎች ለቦርድ የሚያቀርቡት ሃሳብ በአምስት ደቂቃዎች ይገደባል።

## XII. የቀን መቁጠርያ/ካለንዳር

የፋሲሊቲ አጠቃቀም እቅድ በሞንትጎመሪ ካውንቲ በየሁለት ዓመቱ CIP የሚከናወን እና በዓላትን እና ሌሎች መደበኛ ያልሆኑ ሁኔታዎችን ለማካተት የሚከተለዉን ካላንደር በመጠበቅ ማስተካከያዎች ይደረጉበታል።

| | |
|---|---|
| MCPS ሠራተኞች ስለፀደቀው CIP መረጃዎችን ለመለዋወጥ እና ስለ መጪው CIP ወይም CIP ማሻሻያዎች ጉዳዮችን ለማገናዘብ MCCPTA፣ ከአካባቢ ምክትል ፕሬዚደንቶች፣ የክላስተር አስተባባሪዎች፣ እና PT(S)A ተወካዮች ጋር ይገናኛሉ። | ሰመር |
| ለአዲሱ CIP አጠቃቀም የመከፈል አቅምን በሚመለከት የወጪ አቅምን በካውንቲው ካውንስል መመሪያ ይወሰናል። | ጎደሎ ቁጥር ያላቸው የበጀት ዓመታት አክቶበር-መባቻ ላይ ሲሆን |
| MCPS ሠራተኞች የምዝገባ ሁኔታዎች እና የፕላን ዝግጅት ጉዳዮችን ለቦርዱ ያቀርባሉ። | ፎል |
| ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ማካለል፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ አመዳደብ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም መጣመር፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ አጠቃቀም ጋር የሚገናኙ የበለጠ ጊዜ የሚያስፈልጋቸው የህዝብ አስተያየት የሚሹ ጉዳዮችን የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንደንት አዘጋጅቶ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው አስተያየቶችን ለቦርድ ያቀርባል። | ፎል |
| የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንት ዓመታዊ የካፒታል በጀት እና የስድስት-ዓመት CIP ወይም CIP ማሻሻያዎችን በማዘጋጀት አስተያየቶችን ለቦርድ ያቀርባል። ከዚህ አቅርቦት ጋር በማያያዝ የቦርድ አባላት አማራጮች ሊያቀርቡ የሚችሉበት ቦርዱ አንድ የስራ ክፍለጊዜ ሊወስድ ይችላል። | ፎል |
| ስለ CIP ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የስራ ክፍለጊዜዎችን በማካሄድ ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም መጣመር፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ አጠቃቀም ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በሚመለከት ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በቀረቡት ሪኮመንድሽኖች ላይ ሌሎች አማራጮችን ጭምር ያገናዝባል። | ከኖቬምበር መግቢያ እስከ ኖቬምበር አጋማሽ |
| ስለ CIP ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ የትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ አጠቃቀም ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን በሚመለከት በቀረቡት የውሳኔ ሀሳቦች ላይ ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የማህበረሰብ አስተያየት መስጫ ክፍለጊዜዎችን ያካሄዳል። በአንድ የስራ ክፍለ ጊዜ ከቀረቡት አማራጮች አንዱ አማራጭ በቦርዱ ከተለየ በኋላ፣ በአማራጩ ላይ የማህበረሰብ አስተያየት ለመቀበል የተለየ የአስተያየት መስጫ ክፍለጊዜ መካሄድ አለበት። | ኖቬምበር አጋማሽ |
| ስለ ካፒታል ባጀት፣ CIP፣ ማሻሻያዎች፣ እና ማናቸውም የቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ትምህርት ቤት መዘጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ የፋሲሊቲ አጠቃቀም ጉዳዮችን በሚመለከት ቦርዱ እርምጃ ይወስዳል። | ከኖቬምበር አጋማሽ እስከ ኖቬምበር መገባደጃ |
| የካውንቲው ስራ አስፈጻሚ እና የካውንቲው ካውንስል ከቦርድ የቀረበለትን የካፒታል ባጀት እና CIP ተቀብሎ ይገመግማል። | ዲሰምበር 1 |

| | |
|---|---|
| የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ የቀረበለትን የካፒታል ባጀት እና CIP ወይም ማሻሻያዎችን ለካውንስሉ ያቀርባል። | ጃንዋሪ 15 |
| የካውንቲው ካውንስል ስለ CIP ከህዝብ የሚቀርቡ አስተያየቶችን ያዳምጣል። | ፌብሩወሪ እስከ ማርች |
| የካውንቲ ካውንስል ከቦርድ የቀረበለትን እና የካውንቲው ሥራ አስፈጻሚ አስተያየት የተሰጠበትን የካፒታል ባጀት እና CIP ይመለከታል። | ማርች እስከ ኤፕረል |
| በትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንተንዳንት የሚዘጋጁ ማናቸውም የእቅድ ጉዳዮች፣ የቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ት/ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር፣ እና ሌላ የፋሲሊቲ አጠቃቀም ጉዳዮችን እና/ወይም CIP ማሻሻያ(ዎች) አስፈላጊ ከሆነ ቦርድ እንዲመለከታቸው ይፋ ይቀርባሉ። | ፌብሩወሪ-ኢጋማሽ* |
| ስለ ቦታ መረጣ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ ከፋሲሊቲ አጠቃቀም ጋር ስለሚገናኙ ጉዳዮች በቀረቡ አስተያየቶች ላይ፣ አስፈላጊ ከሆነ ቦርዱ አንድ ወይም የበለጠ የሥራ ክፍለጊዜ በመመደብ አማራጮችን ይመለከታል። | ከፌብሩወሪ መግቢያ እስከ ማርች ኢጋማሽ* |
| አስፈላጊ ከሆነ እና ቦርዱ ሌሎች አማራጮች ካሉት አንድ ወይም የበለጠ የህዝብ አስተያየት መቀበያ ሁነቶችን ያካሄዳል። | ፌብሩወሪ መገባደጃ |
| ስለ CIP የቀረቡ ምክረሃሳቦች እና/ወይም የቦታ ምርጫ፣ የትምህርት ቤት ክልሎች፣ ጂኦግራፊያዊ የተማሪ ምርጫ ምደባ እቅዶች፣ ትምህርት ቤት መዝጋት እና/ወይም ማጣመር፣ ወይም ሌላ የፋሲሊቲ አጠቃቀም ጉዳዮችን በሚመለከት በቀረቡት የተለያዩ ሃሳቦች ላይ ቦርዱ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። | ኤፕረል |
| የካውንቲው ካውንስል የስድስት-ዓመት የካፒታል ባጀት እና CIP ያፀድቃል። | ሜይ-መጨረሻ |
| የክላስተር PT(S)A ተወካዮች ስለ መጪው CIP ወይም CIP ማሻሺያዎችን በሚመለከት በት/ቤቶቻቸው ላይ ስለሚያደርሱት ተፅእኖ ኣስተያየቶችን ለት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ያቀርባሉ። | ጁን |
| የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት በዚህ ወቅት ትምህርት ቤቶችን የሚመለከቱ ድርጊቶችን (ማስተር ፕላን) እና ስለ ወደፊት አስፈላጊ ነገሮች የተቀናበረ መግለጫ ያዘጋጃል። | ጁላይ |

*አስፈላጊ ከሆነ ለሌላ ጊዜ የሚተላለፉ ጉዳዮች እና እቅዶች ለባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ተጨማሪ ጊዜ ለመስጠት የጊዜ ሠሌዳው ሊሻሻል ይችላል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Code of Maryland Regulations §13A.01.05.07 and §13A.02.09.01-.03; Charter of Montgomery County, Maryland, Section 305; Montgomery County Code, Chapter 20, Article X, §§20-55 through 20-58

**ስለ ደንቡ ታሪክ፡-** የመጀመሪያ ደንብ ጁን 1, 2005፣ ማርች 21, 2006 ተሻሽሏል፤ ኦክቶበር 17, 2006 ተሻሽሏል፤ ጁን 8, 2008 ተሻሽሏል፤ ጁን 6, 2015 ተሻሽሏል፤ ኦክቶበር 11, 2017 ተሻሽሏል፤ ሜይ 2, 2019 ተሻሽሏል፤ ኦክቶበር 8, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

(a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣

(b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም

(c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</td><td>MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ ***</td></tr>
<tr><td>Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 | 504@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 | DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ***</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 | TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@ mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025